ፓኖራማ ቁጥር 62

የትዝብት አድማስ

መጋቢት 1 ቀን 2001 ዓም

## ማስወገድን አታንሱ ÷አገር ትፈርሳለች

## ወያኔን አትንኩ ÷ ጦቢያ ትጠፋለች

"ጉድ ሳይሰማ ህዳር አይታጠንም"ሲባል የነበረው ባህላዊ አነጋገር ለካ ከዕውነት የራቀ አልነበርም ጃል! በምንሊክ ግቢ የተከማቹት የዘረኛ ሥርዓት አራማጆች ሁሉንም የፕሮፓጋንዳ ውሽካታ አውርተው አውርተው ቋቱ ሲነጥፍባቸው ÷ ሰሞኑን ደግሞ አንድ የማታለያ ማስደንገጫ ማስወራት ጀምረዋል። ይኸውም "ወያኔ ከሌለ÷ ዜጎቿ ይበታተናሉ÷ ሀገሪቱም ትጠፋለች " የሚል ማስፈራሪያ ነው። ለዚህ ፍሬ ፈርስኪ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ዕቅድ አውጭዎቹ÷ከነርሱ ጉያ ተሸልቅቀው የወጡት ሰየ አብረሃ÷ገብሩ አስራትና ግብረ-አበሮቻቸው ናቸው። ተከታዮቻቸውም ከእነርሱ ጋር በአጃቢነት የተኮለኮሉ ተስፈኞች÷የመድረክ ዳስ ለመቀለስ ደፋ ቀና እያሉ እንደሚገኙ ዛሬ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተደበቀ እንዳለ ሆነ ግልፅ ነው። የወያኔ አፈ-ቀላጢዎች ይህንን ቢሉ አይፈርድባቸው ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ልብ ጠልቀን አውቀነዋል ። አዕምሮውንም ፈትሸን አግኝተነዋል ። ለአለፉት አስራ ስምንት ዓመታትም እንደ ገል እየቀጠቀጥን እንደ ሰም እያቀለጥን መግዛት ችለናል ። ሀገሪቱንም ያለአንዳች ተቀናቃኝና መሰናክል እንዳሻችን እያደረግናት እንገኛለን ብለው ምፀት ተናግረዋል። ተመፃድቀዋልም። ልብ በል የኢትዮጵያ ሕዝብ ! አስተውል አንተ ትውልድ! የድፍረታቸው ድፍረት የተመሰረተው ÷ የኢትዮጵያን ሕዝብ ማንነት በቅጡ ካለማወቅ የመነጨ ድርቅና ስለሆነ÷" የአገሪቷ ቀሪው ሰው÷ተስማምቶና ተማምኖ ÷ ተባብሮና ኅብረት ፈጥሮ÷ መሪ አውጥቶ እኛን ይቋቋመናል ብለን አንሰጋም " እስከ ማለት ደርሰዋል ። በመሆኑም ÷" የእኛን የዘር ፖለቲካና ፖሊሲ አምኖ በመቀበል ከመገዛት በስተቀር ሌላው ሁሉ የሚያዋጣ አይደለም ። የማሰወገድ ፖለቲካና አስተሳሰብ ያረጀ-ያፈጀ አመለካከት በመሆኑ÷ወያኔን

እናስወግድ የሚለው ጥሪ ወደ ደም መፋሰስ የሚያመራና አደገኛ አዝማሚያ ስለሆነ ፥ የሚያዋጣው፥ እየተገዙ “መታገል”፥ እያጎበደዱ መኖር ብቻ ነው ። ብለው ደምድመዋል። ደጅ ጠኝዎቹና ተስፈኞቻቸው ደግሞ፥

“ እርሱ ያመጣውን እርሱ እስኪመልሰው፥
እያጎበደዱ በሰላም መኖር ነው።”

እያሉ የተስፋ መቆረጥ ሙሾ ይደረድራሉ።

ይህ የባንዳዎችና የተንበርካኪዎች ዝማሬ ፥አሳፋሪ ብቻ ሳይሆን፤ ትጥቅ አስፈች ጭምር መሆኑንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ደህና አድርጎ ተረድቶታል ። ወያኔ ካልተወገደ የጤና እንቅልፍ እንደማያገኝም በሚገባ ያውቀዋል ። በመሆኑም፥ የአምባገነኖችን አገዛዝ አስወግዶ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መተካት፥ የወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ስትራተጂ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአለፉት አርባ ዓመታት የተፈራረቁትን አምባገነን ሥርዓቶች መስዋዕት ከፍሎ ማስወገዱ የቅርብ ትዝታው ስለሆነ ፥ ሰፊ ዝርዝር ማቅረብ የሚያስፈልገን አይደለም ። የዓፄውን ሥርዓት ታግሎ አስወግዷል። የወታደራዊውን አምባገነን ሥርዓትም አይከፍሉ መሥዋዕት ከፍሎ አስወግዷል ። የወያኔውን ዘረኛና ከፋፋይ ሥርዓት ማስወገዱ አይቀሬ ነው ። የዓፄውም ይሁን የወታደር፥ የዘረኞችም ይሁን የማነኛውም ሥርዓት አምባገነን እስከሆነ ድረስ መወገድ አለበት። የወያኔዎቹ ዘረኛ ሥርዓት በአማላጅና በማስፈራራት ወይም፥ በቁልምጫ ሊወገድ ከቶ አይችልም ። በመሆኑም ፥ በማነኛውም ጊዜ ከመወገድ የሚድንበት አንዳች ምክንያት አይኖርም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አምርሮና ተባብሮ ከተነሳ ደግሞ ወያኔን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን ፥ ሀገሩን በማልማት ረገድ ተዓምራዊ ውጤት እንደሚያስመዘግብ አንዳችም ጥርጣሬ ሊኖር አይችልም ።

አምባገነን መወገድ አለበት ሲባል ፥ ግለሰቦችን ከሥልጣናቸው ማስወገድ ብቻ ማለት አይደለም:: ሥርዓቱን እስከ አራማጆቹ አሽቀንጥሮ መጣል ማለት እንጅ! አባይን በስየ ፥መለስን በገብሩ ፥ መበወዝ ማለት አይደለም :: ጥርሱ የዶለደመውን አሮጌ ዘረኛ፥በአዲስ ጥርስ በአገጠጠ አፍለኛ ዘረኛ መተካት ማለትም አይደለም :: የወያኔ ሁለንተናዊው የዘረኝነት ሥርዓትና ፖሊሲው፥ "ህገ መንግሥቱ" እርሱንም መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦችና ህግጋት ፥ የስለላ መዋቅሮችና የወንበዴ መረቦች ፥ የነፍስ ግድያ ማሰለጠኛዎችና የዓጋዚ -ጌስታፖ አሸባሪና ነፍሰ-ገዳይ ፈጥኖ ደራሽ ተወርዋሪ ጦር፥የፌዴራል አፋኝና ጨፍጫፊ ቡድን የስውር ማሰሪያ ቤቶችና የማሰቃያ ጉድጓዶች ሁሉ የዘረኞች ሥርዓት ዋልታና ማገር ናቸው:: እነኝህ የሥርዓቱ መሳሪያዎች ሁሉ እንዳሉ ሆነው መለስንና ግብረ-አበሮቹን ብቻ በማግለል ፥ በስየ- ገብሩ ቀንደኛ የዘረኞች ቡድን ተክቶ የኢትዮጵያን ስር የሰደደ ችግር እንፈታለን ብሎ መዳከር፥ ሌላው ቢቀር፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ የአዕምሮ ብስለትና የማሰብ ችሎታ መሳደብ ነው:: ከዚህም በቀር፥ መንግሥትን መንግሥት የሚያሰኙትን ባኅርያት፥ ይዘትና ተግባራትን በመሠረታዊ መልኩ አለመገንዘብ ነው::

የፖለቲካ ሳይንስ ጠበብት እንደሚሉት ፥ የማነኛቸውም አምባገነን አገዛዞች የዕድሜያቸው ማስረዘሚያና የሥልጣናቸው ማጠንከሪያ መሠረቶቹ የመጨቆኛ መሳሪያዎቻቸው ናቸው:: ዋናው መሠረቱ፥ ለአገዛዛቸው ድልዳል የሚሆነውን ህግ ማውጣት ነው :: ይህንንም ህግ በመመርኮዝ፥ ፍርድ ቤቶች፥ ፖሊሶች ፥ የፀጥታ ሰራተኞች፥ የወንበዴ ቡድኖች፥ የማጎሪያ ጣቢያዎች፥ ታጣቂ ነፍሰ -ገዳዮች፥ማሰመራትና የሕዝቡን አመፅ ለመከላከል ወታደር ማስልጠን ናቸው:: የዓለምአቀፍ ኅብረተሰብን ለማወናበድ ደግሞ የእምቧይ ካብ የሆነውን የተኮላሸ ፓርላማ ጠፍጥፎ መስራት ነው:: የወያኔን ማንነት ያልተረዱትና እራሳቸውንም ለማታለል የተዘጋጁት በወያኔ የምርጫ ውድድር ገብተን እንሞክረው ብለው ለባዘኑትም የዋሆች ፥መለስ ዜናዊ፥" በደማችን ያገኘነውን ሥልጣን በምርጫ ካርድ አናስረክብም" ሲል እቅጩን ነግሯቸዋል::ይህ ፅንፈኛና ተስፋ ቢስ ዘረኛ

ቡድን ምንም ምን ቢሆን ራሱን አሻሽሎ ለጥገና ለውጥ ፍንጭ ሊያሳይ እንደማይችል እንኳንስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ፥ ባዕዳን አለቆቹም በሚገባ ተረድተውታል። ታዲያ ይህ ቡድን ካልተወገደ ማን ሊወገድ ይገባል ?

በአሁኑ ወቅት መድረክ በሚል ስም ለመሰባሰብ የሚፍጨረጨሩት ሳልሳዊ የወያኔ ቡድኖች ፥ ልክ ከሃያ ዓመታት በፊት መለስ ዜናዊ እንደ ለማኝ ጥሬ በየቦታው የተጠራቀሙትን ሰብስቦ ከወያኔ ጋር በመጠፍጠፍ ኢሕአዴግ በሚል ጭምብል ለውሶ ሥልጣን ለመያዝ እንደበቃ ሁሉ፥ የአሁኖቹ ደግሞ፥ መለስን እናውርድና ሥልጣኑን እንድንረከብ ተባበሩን ብለው የማሰባሰቢያ መድረክ ፈጥረናል እያሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዐይንህን ጨፍንና ዳግመኛ እናሞኝህ እያሉት ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ መለስንና ግብረአበሮቹን የሚያያቸው ከዘረኛ አገዛዛቸው ፥ ከዕኩይ ባኅርያቸውና ከአጥፊ ሥራቸው ጋር እንጅ በተናጠል አይፋረዳቸውም ። የወያኔን ግለሰቦች የሚጠላቸውና የሚታገላቸው፥ ባዕዳን ጠላቶች ሆነው ሳይሆን የወገን ጠላቶችና ብሔራዊ ወንጀለኞች ስለሆኑበት ነው። ለዚህም ነው እነርሱ እስከ አጥፊ ጎሰኛ ሥርዓታቸው መወገድ አለባቸው ብሎ በመወሰን አምርሮ የሚዋጋቸው።

የወያኔ መሪዎች፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ እነርሱ ያለውን አቋም ፥ ማንም ሳይነግራቸው በሚገባ ያውቁታል ። ይህንን ግንዛቤ ያስጨበጧቸው ከእነርሱ በፊት የነበሩት ሁለት ተፈራራቂ አምባገነን ሥርዓቶች ናቸው።
" የምንወደውና የሚወደን ሕዝባችን " ሲል የነበረው የዓፄው ሥርዓትና፥ "ሞቴን ከሰፊው ሕዝብ ጋር ያድርገው" እያል ጠርሙስ ሲሰብር የነበረው ዛራም ደርግ ፥ ፍጻሜያቸው ምን እንደሆነ ፥መለስና ጓደኞቹ ያውቁታል ። ማወቅም ብቻ ሳይሆን አወዳደቃቸውን ለማሳመር ትምህርት ለመቅሰም በመፍጨርጨር ላይ ናቸው።"መለበሚያ አታድርገኝ፥ ግን ደግሞ ማለበሚያም አትንሳኝ "የሚለውን ይትበሃል ለመገንዘብ ሰኔና ሰኞ ይዞላቸዋል ። ይህንን መገንዘብ ለጮሌነታችን ጠቅሞናል ለማለት ቢችሉም፥ አንድ ትልቅ የታሪክ

ሀቅ ግን ሊያስተውሉ አልቻሉም:: ይህም÷ ከእነርሱ በፊት የነበሩት ሁሉቱም ጨቋኝ ሥርዓቶች÷ እንደ ሥርዓት የተወገዱ መሆናቸውን ነው:: ወያኔዎቹ ÷ ይህንን የታሪክ ሀቅ ሊቀበሉ ቀርቶ ሊያስቡትም እንኳን አይፈለጉም:: ታዲያ ዛሬ የእነርሱ አሽቃባጮችና የበላይ ጠባቂዎቻቸውም ጭምር÷ወያኔን ማስወገድ ማለት ሀገሪቱ እንድትፈርስ ማድረግ ነው በማለት የቀቢፀ-ተስፋ ፕሮፓጋንዳ ይነዛሉ:: ይህም ከንቱ የፖለቲካ ስሌት ÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገሩን ወዳድ ስለሆነ "ሀገሬ ከምትፈራርስብኝስ ÷ወያኔ ዘለዓለም ይንገስ " በማለት÷ሰጥ ለጥ ብሎ ይገዛል ከሚል ከታሪክ ሃቅ ጋር የተጋጨ ድምዳሜ ለመድረስ ተገድደዋል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ አያሌ የውስጥና የውጭ ጠላቶችንና ገዥዎቹን በህብረት እየተቋቋመ ቆይቷል::መከራና ደስታውንም በጋራ እየተካፈለ አብሮ ኖሯል :: የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወትና ታሪክ ከወያኔ በፊት ነበር:: ወደፊትም ወያኔን አስወግዶ በአንድነቱ የጋራ ታሪኩንና ሕይወቱን አብሮ በመኖር ይኖራል :: ወያኔ ከሌለ ነገር ተከተተ የሚባል የልጆች ተረት ተርት የወያኔና የተስፈኞቹ ጨዋታ÷ለኢትዮጵያ ሕዝብም እንደ ተረት ተረት ነው:: ይህንን ፌዝ የሚያቀነቅኑትንም ያፌዝባቸዋል::ወያኔንም ከማስወገድ ለደቂቃ እንኳን አይቦዝንም:: የወቅቱ ዝማሬውም:-

ይወገዳል እንጅ ምነው አይወገድ ÷
በሁለንተናዊው በአስፈላጊው መንገድ!!!!

የሚል ብቻ ነው :: ሀገርን ለማዳን ወያኔን ከነሥርዓቱ ማስወገድ ፤ መጣልና ማንኮታኮት ቋሚና ዋና ትግባር ግዳጅ ነው :: ወያኔን በሌላ ወያኔ መተካት ሊታሰብም የሚችል አይደለምና በዚህ መስክ ሶምሶማ ሊረግጡ ደፋ ቀና የሚሉትም ከመሰበር ሌላ ዕጣ -መጨረሻ አይኖራቸውም :: ባንዳና አንጃ ግን ልማዱ ነውና ከታሪክ ትቢያ መጣያ ሲወድቅ የምናዝንለት ሊሆን አይጠበቅም ::

የኢትዮጵያ ትንሳዔ በወያኔ አገዛዝና ሥርዓት መቃብር ላይ የሚያብብ ነው::